# + ing ... ብንጨምርስ?

## ጠቃሚ ምክሩን ይማሩ

**ቃል ምረጥ/ጭ:** ልጅዎ እያነበበ/ች የፊት፣ የኋላ ቅጥያ ያላቸውን ቃላት፣ ወይም -ed እና -s የሚያልቁ ቃላትን ፈልጉ። ወይም የፊት ቅጥያ (መጀመሪያ ላይ) ወይም የኋላ ቅጥያ (መጨረሻ ላይ) መጨመር የምትችሉባቸውን።

**የኋላ እና የፊት ቅጥያ ጨምሩ እና/ወይም ቀንሱ:** የልጅዎን ሙከራ አበረታቱት/ቷት። ትርጉም የሌላቸውን ቃላት መፍጠር ይችላሉ! ትርጉም የሌላቸው የተፈጠሩ ቃላት ቢሆኑም እንደ ትክክለኛ ቃላት ተመሳሳይ የድምፅ አወቃቀር አላቸው። ልጅዎ የድምፅ ስርአትን እንዲለማመድ ይረዳሉ።

**ቃሉ እንዴት እንደሚቀየር ተወያዩ:** የቃሉን አቀያየር ተወያዩ። ለምሳሌ አዲስ ትርጉም የሚሰጥ፣ ወይም ከግስ ወደ ስም የሚቀየር፣ ወይም -s በመጠቀም ብዙ ሊሆን ይችላል።

### ጠቃሚ ምክሩ ለምን አስፈለገ?

እንደ አንባቢ ለማደግ ልጅዎ አዲስ፣ አሳሳች ቃላትን ለመረዳት የተለያዩ “መሳሪያዎችን” መጠቀም አለበት/ባት። መጀመሪያና መጨረሻን ማየት አንባቢያን ቃልን የሚረዱበት አንድ መሳሪያ ነው።

## ልጅዎን ይጠይቁ

*ትናንሽ ልጆች*

የቃሉን መጨረሻ ትርጉሙን ለመረዳት እንደ ፍንጭ እንጠቀመው። መጨረሻው -s ሲሆን ቃሉ ብዛትን እንደሚያሳይ እናውቃለን።

ቃሉ ላይ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ ብንጨምርበት ቃሉ እንዴት ይቀየራል?

*ትላልቅ ልጆች*

ቃሉ ላይ የኋላ ቅጥያ እንጨምር። -ness ጨምረን ቃሉን ስም ብናደርገውስ?

ቃሉ ላይ የፊት ቅጥያ እንጨምር። un- ማለት “ተቃራኒ” ወይም dis- “አለመሆን” የሚለውን ብንጨምርስ?

ቃል ላይ የፊት ወይም የኋላ ቅጥያ ብትጨምር/ሪ የቃሉ ትርጉም እንዴት ይቀየራል? የአዲሱ ቃል ትርጉም ምንድን ነው?

አርፍተነገር ውስጥ መጠቀም ትችላለህ/ያለሽ?

... ብንጨምር ወይም ብንቀንስስ?

ይሄ ትርጉም የሌለው ቃል ግን ምን ማለት ሊሆን ይችላል? ለምን?

## በመዝናናት ተለማመዱ

“ምድቦች” ተጫወቱ።

ምድብ ምረጡ እና በምድቡ ውስጥ ልታስገቡ የምትችሉትን ያህል ቃላት ተናገሩ። እንደ “ፍራፍሬ” ያለ ትልቅ ሊሆን ይችላል ወይም እንደ “ባስ ላይ የምታገኟቸው ነገሮች” ያለ የበለጠ ትኩረት ያለው ሊሆን ይችላል። ውድድር ማድረግ ትችላላችሁ (በመደቡ ውስጥ የሚካተት ቃል ማሰብ ያቃተው ይሸነፋል) ወይም ለመዝናናት ተጫወቱ።

በፊት ወይም በኋላ ቅጥያ መጫወት ከፈለጋችሁ ምድቡን “በ pre- የሚጀምሩ ቃላት” ወይም “ስም የሆኑ ቃላት” (አብዛኞቹ መጨረሻቸው -ness ወይም -ion ነው)።